ሀብ ረተሰብ ሳይንስ
5ኛ ክፍል

ኑር አፍሪካ አካዳሚ



የክለሳ ማስተዋሻ

አዘጋጅ : አብዱ አሊ

ጥቅምት 2013

ምዕራፍ አራት

ህዝባዊ ጉዳዮች

ህዝባዊ ነክ ጉዳዮች

- **<u>ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች</u>**
- ኤች አይ ቪ የቫይረሱ መጠሪያ ሲሆን ኤድስ ደግሞ የበሽታው መጠሪያ ነው።
- ቫይረሱናበሽታው በአንድ ላይ ኤች አይ ቪ ኤድስ በሚል መጠሪያ ይታወቃል።


ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት

- ልማዳዊ ድርጊቶች የአንድ ህብረተሰብ ባህል አካል ናቸው።
- ባህል ደግሞ የሰዎች የመኖር ጥረቶች ድምር ውጤት ነው።
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ድርጊቱ የሚፈፀምባቸውን ግለሰቦች ጤና የሚያቃውሱ፣ዘላቂ ህመም ወይም ሞት ሊያስከትሉ ይችላሉ። በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ላይ ምጣኔ ሀብታዊ ና ማህበራዊ ህይወት ላይ ጫና ይፈጥራሉ።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

- ጠለፋ
- እንጥል መቁረጥ ወይም መቧጠጥ
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ ወይም ያላቻ ጋብቻ
- የሴት ልጅ ግርዛት
- ግግ ወይም ወተት ጥርስ ማስወጣት
- የአካል ላይ ጠባሳዎች(Tatoo) ወዘተ.....ናቸው።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ መስፋፋት



- ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ የሚተለለፍባቸው አራት ዋና ዋና መንገዶች
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም
- የደም ልገሳ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ያልተመረመረ ደም መስጠት
- ቅድመ ወሊድ፣በወሊድ ጊዜ ና ከወሊድ በጎላ ቫይረሱ በደሟ ካለ እናት ወደ ልጅ
- በደም በተበከሉ ስለታም ነገሮች በጋራ መጠቀም ናቸዉ።

የኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ መስፋፋት መንስኤ

- በጋብቻ ጊዜ ቅድመ ምርመራ አለማድረግ
- ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም
- የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መስፋፋት

የኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ መስፋፋት የሚያስከትለው ተፅዕኖ

- ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ በአለማችን በከፍተኛ ደረጃ ገዳይ ከሆኑ በሽታዎች አንዱ ነው።
- ለቫይረሱ ተጋላጭ ከሆት የማህበረሰብ ክፍል ደግሞ ወጣትና ጎልማሳ፣የተማረ ና የሰለጠነው የማህበረሰብ ክፍል ነው።
- የሀገር ምጣኔ ሀብት ላይ ችግር ይፈጥራል
- ህፃናትን ለጎዳና ህይወት ያጋልጣል
- አረጋውያንን ያለጧሪ ቀባሪ ያስቀራል

የህፃናት መብት

- ህፃናትን ለሀላፊነት ለማብቃት ከሚፈፀሙ ተግባራት መካከል ዋነኛው የህፃናትን መብት ማክበር ነው።

የህፃናት መሰረታዊ መብቶች

- የመጠሪያ ስም ወይም ዜግነት የማግኘት መብት
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነፃ የማግኘት መብት
- በአካል፣በአእምሮና በማህበራዊ ረገድ የሚያስፈልጋቸውን ዕድሎችና ቁሳቁሶች የማግኘት
- ከማንኛውም አይነት ጭካኔ፣ እንክብካቤ አልባነትና ምዝበራ፣ ከጉልበት ብዝበዛ ነፃ የመሆን
- ከአካል ቅጣት ነፃ የመሆን
- ዕድሜያቸው ለስራ ሳይደርስ ለከባድ ስራ አለመቀጠር ወዘተ ናቸው።
- የህፃናትን መብት ለማስከበር የቆሙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች **ዮኒስኮ** እና **ዮኒሴፍ (UNESCO andUNICEF)**ናቸው።
- **ዩኒስኮ** ማለት የተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሣይንስና የባህል ድርጅት ሲሆን **ዩኒሴፍ** ማለት ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የህፃናት የአደጋ ጊዜ ፈንድ ወይም ገንዘብ የሚረዳ ድርጅት ማለት ነው።

ድንገተኛ አደጋና ደህንነት

- በአገራችን በገጠሩም ሆነ በከተማዎች ዋና ዋና የአደጋ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው።
- የተሸከርካሪዎች አደጋ
- የእሳት አደጋ
- የጎርፍና የውሀ ሙላት አደጋ
- ከቤትም ሆነ ከውጭ ሊያጋጥም የሚችል አደጋና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተፅዕኖዎች

የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት

- መንግስት ለዜጎች ከሞላ በጋራ የሚያቀርባቸዉ አገልግሎቶች ማህበራዊ ግልጋሎቶች ይባላሉ።
- ለምሳሌ፡ የጤና አገልግሎት
- የትምህርት ቤት አገልግሎት
- የመኖሪያ ቤት አገልግሎት
- የንፁህ ዉሀና የሳል አቅርቦት አገልግሎት
- ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ይፈጥራል።
- የህዝብ ብዛት ማለት በአንድ አገር ውስጥ በአንድ የተወሰነ ወቅት የሚኖሩ ሁሉም ሰዎች ቁጥር ማለት ነው።

የእርሻ መሬት እጥረት

- የህዝብ እድገት ጫና በኢትዮጵያ ሁለት ዓበይት ችግሮችን አስከትሏል።
- የማህበራዊ ግልጋሎት እጥረ
- የእርሻ መሬት እጥረት
- መልካም አስተዳደር፣ የህግናት መብትና ደህንነት

መልካም አስተዳደር

የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች

- ተጠያቂነት
- ግልፅነት
- የህግ የበላይነት
- ሙስናን መዋጋት



የመኪና አደጋ

- በአንድ በስፋት የሚነገር በሁሉም ስፍራ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ እንደ መመሪያ ሊወሰድ የሚገባ የብልሆች አባባል መካከል እርምጃችሁን አስተውሉ፣ጠንቀቅ በሉ፣አስቡ ከዚያም ፈፅሙ የሚለው ነው።

የእንስሳት አደጋ

- የእንስሳት አደጋ ከፍተኛ የህይወትና ንብረት አውዳሚ ነው። እንስሳት አደጋ መከሰት ምክንያት የግንዛቤ ማነስና ግደለሽለት ናቸው። በቀላሉ ሊጠቀሱና የእሳት አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ እንዴ ነዳጅ ዘይት ውጤቶች፣ ደረቅ ቅጠልና እንጨት፣ በመስክ ላይ ለመዝናናት ከሚቀጣጠል እሳት፣ የተቀጣጠለ ከሰል፣ ያለጥንቃቄ የሚወረወር ርችት፣ የተለኮሰ የክብሪት እንጨትና የሲጋራ ቁራጭ ናቸው።

የጎርፍና የውሀ ሙላት አደጋ

- የጎርፍና የወንዝ ዉሀ ሙላት በአብዛሀኛው ጊዜያዊና አጭር ጊዜ የሚከሰቱ አደጋዎች ናቸው።

የእንስሳት ትንኮሳ

- ውሻን የመሳሰሉ የቤት እንስሳት አደገኞች ናቸወ።
- ንክሻው የእብድ ውሻ በሽታ(rabies)ሊያስከትል ይችላል። የዚህ አይነት አደጋ ሲያጋጥም በፍጥነት የህክምና አገልግሎት ማግኘት ያስፈልጋል።